የወ/መ/ቁጥር 169738

የልደታ ምድብ 6 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 15 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ አያና አበበ ቀረቡ

ተከሳሽ፡ አቶ ገ/ፃዲቅ ሲራኒ በሽር - ከጠበቃ አበበ በለው ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ መጋቢት 03 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 559(2) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሌላ ሰው አካል ወይም ጤንነት ላይ በቸልተኝነት ሚየዝያ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 11፡30 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 04 ልዩ ቦታው ካራቆሬ ናትራን ከባንያ ከፍ ብሎ ሞቢል አካባቢ(ፍንፍኔ ማተሚያ ቤት አካባቢ) ኮድ 2-34671 የሆነ መኪና ከካራቆሬ ወደ አየር ጤና እያሽከረከረ እያለ የግል ተበዳይ ወ/ሮ አልማዝ አበራን ከእግረኛ መንገድ መጓጓ መንገድ ላይ ገጭቶ በጭንቅላቷ፤ በግራ ትከሻዋና የግራ እግሯ ላይ የመቁሰል እንዲሁም በወገቧ አካባቢ በሚገኙ አጥንቶች ላይ የዳሌ አጥንት ስብራት ጉዳት በማድረሱ በፈፀመው በቸልተኝነት የሚፈፀም የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን ፈፅሜያለሁ፤ ነገር ግን ጥፋተኛ አይደለሁም ብሎ ክዶ በመከራከሩ የዐ/ሕግ ምስክሮች ቀርበው ተሰምተዋል። አንደኛ የዐ/ሕግ ምስክር/የግል ተበዳይ/ ቀኑን፤ ሰዓትና ቦታውን በትክክል ገልፀው ተከሳሽ ሲያሽከረክር በነበረው መኪና ታክሲ ለመጠበቅ ለዋናው መንገድ ሁለት ሜትር ርቄ በነበረት ሰዓት ገጭቶኛል፤ በዚህም ምክንያት በአካሌ ላይም ጉዳት ደርሷል በማለት አስረድተዋል። ሁለተኛ ምሰክር ደግሞ የሙያ ምስክር ማለትም የትራፊክ እንቅስቃሴ ባለሙያ መሆናቸውን ገልፀው፤ በተጠቀሰው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ በክሱ ላይ በተጠቀሰው ተሽከርካሪ የግል ተበዳይን ተከሳሹ ጥፋት በሆነ ቸልተኝነት በመንገድ ቀኝ በኩል ሳለ ገጭቶ ጉዳት አድርሷል ሲሉ መስክረዋል። በዚህም መሰረት ተከሳሽ ድርጊቱን መፈፀማቸውን ያመኑ ሲሆን፤ አሁን በሁለቱ ምስክሮች ጥፋተኛ መሆናቸው የተረጋገጠ ስለሆነ፤ ጥፋተኛ አለመሆናቸውን የመከላከያ ማስረጃ አቅርበው እንዲከላከሉ በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዘዋል። ተከሳሽም እከላከላለሁ ብለው ቀጠሮ ከወሰዱ በኋላ በቀጠሮ ቀን

የመከላከያ ምስክሮቻችን ለማቅረብ አንችልም በማለት በችሎት ገልፀዋል። ከዚህ ለመገንዘብ የሚቻለው ተከሳሽ ለድርጊቱ መፈፀም ጥፋተኛ አለመሆናቸውን የመከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ለማስተባበል ያለመቻላቸውን ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 559(2) ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ተወስኗል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

ዐ/ሕግ፡ የምናቀርበው የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ የለም፤ ነገር ግን ፍ/ቤቱ ተከሳሽን የሚያርማቸውና የሚያስተምራቸው ቅጣት እንዲወስን በማለት አመለከቱ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 51 ዓመት ነው፤ ትዳርና ስምንት ልጆች ያሉኝ ሲሆን ስድስቱ ልጆች አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸውና በእኔ ስር ሆነው የሚተዳደሩ ናቸው፤ ቡበየዳ ሥራ በወር እስከ ብር ሰባት መቶ ድረስ አገኛለሁ፤ ከአሁን በፊት በወንጀል ተቀጥቼ አላውቅም፤ የግል ተበዳይ ኩበር አንድ ሺህ በላይ ወጪ በማድረግ አሳክሜያለሁ ብለው ማስረጃውን ለፍ/ቤቱ አቅርበው ፍ/ቤቱ ቅጣቱን አስተያየት እንዲያደርግልኝ በማለት አመለከቱ።

ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ሊያሳካ እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ኩበደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሽ አሁን ጥፋተኛ የተባሉበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 559(2) ደረጃ የወጣለት ወንጀል በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና አባሪ 3 መሰረት የተመለከተው ደረጃ 2 ሲሆን ተጓዳኝ መነሻ እርከኑም 6 ነው። ስለሆነም የዚህ እርከን መነሻ ፈቃደ ስልጣን/range/ ከስምንት ወር እስከ አንድ ዓመት እስራት እና እስከ ብር 2,000.00(ሁለት ሺህ ብር) የሚያስቀጣ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ፍ/ቤቱ ቅጣቱን የሚወስነው የተከሳሽን የትምህርት ደረጃና ዕድሜ ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለሆነ፤ ይህን መሰረት በማድረግም መነሻ ቅጣቱ አስር ወር ቀላል እስራት እና ብር 1200.00(አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) እንዲሆን ነው ያደረገው።

በዚህም መሰረት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ቅጣት ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84 ወይም 85 መሰረት የቅጣት ማክበጃ ያላቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ የመነሻውን ቅጣት እርከኑን ከፍ ሳያደርግ እንዳለ እርከን 6 ን ወስዶታል። በሌላ በኩል ተከሳሽም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 መሰረት በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ያላቀረቡ ስለሆነ ከላይ የተመለከተው እርከንን ፍ/ቤቱ ዝቅ አላደረገውም።

በመሆኑም ከላይ የተመለከተውን የእስራት ቅጣት እና የገንዘብ መቀጮ በመውሰድ ተከሳሽ በአስር ወር ቀላል እስራት እና ቡብር 1,200.00(አንድ ሺህ ሁለት መቶ ብር) መቀጮ እንዲቀጡ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ በአሁኑ ወቅት ስድስት ያህል አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች አባት ስለመሆናቸው በችሎት የገለፁ ሲሆን፤ አስር ቤተሰብም እንዳላቸው ከሚኖሩበት የቀበሌ መስተዳድር የተፃፈ ደብዳቤ ያቀረቡ ስለሆነ፤ የቤተሰቡ የገቢ ምንጭም ስለሆኑ፤ የግል ተበዳይንም በወቅቱ የሚያስፈለጋቸውን ህክምና ተከሳሽ ከብር አንድ ሺህ በላይ ወጪ በማድረግ እንዲታከሙ ያደረጉ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት፤ የተከሳሹ ሕፃናት ልጆች ደግሞ የቤተሰባቸውን የቅርብ ክትትልና እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 36(1) (ሐ) ላይ የተደነገገ ስለሆነ፤ ለሕፃናት ልጆች ሲባል የእስራት ቅጣቱ ከሚፈፀም ይልቅ ለተከሳሽ አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ፀባይና አመላቸው ወደፊት ቢታይ መልካም ስለሆነ የእስራት ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 192 መሰረት በሦስት ዓመት ገደብ አግዶታል።

2 ኛ. ይህ የቅጣት ውሳኔ ሐምሌ 19 ቀን 2002 ዓ.ም ተሰጠ።

3 ኛ. ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 197(2) ለመልካም ፀባይ አመራር ዋስትና ይሆን ዘንድ ቀደም ሲል ለዋስትና ያስያዙት ገንዘብ የሦስት ዓመት ጊዜው

እስኪጠናቀቅ ድረስ ባለበት እንዲቆይ ታዟል። ይፃፍ።

4 ኛ. ተከሳሽ ለመንግስት የፅሀፈት ወጪ ብር 50.00(ሃምሳ ብር) ይክፈሉ፤ ሲከፍሉም መፍቻ ለማ/ቤት ይፃፍ።

5 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

6 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።